# ቡና

## ከበቀለ ገብርኤል (ሲሳይ)

## ሚኒሶታ

በተለያየ ጊዜና በተለያየ አካባቢ ብዙ ቀልዶች ሲደመጡ ይሰማል። በ እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረቱም ይሁን በግል የፈጠራ ችሎታ ብቻ ሲያስቁ፤ ሲያዝናኑ፤ ሲያስተምሩ፤ አንዳንዴም ስያስኮርፉ፤ ሌላ ጊዜም ስያስቆጡና ለጠብ ስጋብዙ ይታያል። ያም ሆነ ይህ ለፅሑፍ እንደ መግቢያ፤ ማብራርያ፤ ወይም ምሳሌ ይምጠቀምባቸው ከቀልድነትና ካዝናኝነት በስተቀር ሌላ ትርጉም እንደሌለው ከወዲሁ ለመግለፅ እሞክራለሁ። ወደ ዋናው ርእስ ከመግባቴ በፊት አጠር ባለች ጭውውት ብጀምር ምን ይመስላችኋል? ምን አልባትም ቀልዱ እግረ መንገዴን ወደ ተነሳሁበት ጽሁፍ መንገድ ከፋች ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

አንድ አባት ምናምን ለመቅመስ ይሉና ወደ ሆቴል ጎራ ይላሉ፡ የምትታዘዘውም ትመጣና

"ምን ላምጣ የኔ አባት ትላቸዋለች?"

"ትኩስ ነገር አላችሁ?" ይላሉ

"አዎን ቡና፤ ሻይ፤ ማክያቶ፤ ቡና በወተት" እያለች ደረደረችላቸው። የገቡበት ሆቴል ትልቅ ስለሆነና ኪሳቸውንም ብዙ ስላልተማመኑ

"ግን ዋጋቸውን ትነግሪኝ ማለቴ ምን ምን የህል ነው" ይሏታል

"ቡና ይህን ያህል ነው፡ ቡና በወተት ደግሞ እንደዚህ ነው" እያለች የሁሉንም ዋጋ ነገረቻቸው፤ ትንሽ አሰብ ካደረጉ በሃላ

"እርጎስ አለ?" አሉ

"አዎን ግን ዎጋው ይህን ያህል ነው" ብላ ስትነግራችው

"አበስኩ ገበርኩ ምነው የሞቀው በኮረንቲ የፈላው እንዲህ ሲረክስ ቀዝቃዛውን ምን አስወደደው" ብለው በመገረም!

"በይ ቡና በወተት አምጭልኝ" የሏታል፡ ትንሽ ቆይታ ይዛ ትመጣለች። ገና ጠረቤዛው ላይ ከማስቀመጧ ብድግ አድርገው ሰኳዎር ጨምረው ካማሰሉ በህላ አፋቸውን እየፈጃቸው ሳያቋርጡ ላፍ አደረጉት። ልጅትዋ በመገረምና በመደንገጥ

"ምነው የኔ አባት ይቸኩላሉ እንዴ!?

"አይ የኔ ልጅ መች አጣሁት ከቀዘቀዘ ደግሞ በእርጎ ዋጋ ልታስከፍይኝ አይደል" ብለዋት እርፍ።

ቡና መቼም ሰፊ ርዕስ ነው ብዙ ተብሎለታል ተፅፎለተል በተለያየ ሀገርም ይሁን ዐለማት እንደ ጊዜ ማሳለፊያም ይሁን ለሱስ ማርኪያ ተጠጥቶዋል እየተጠጠም ነው። በሀገርችንም ቢሆን የውጪ ምንዛሪ ያስገኛሉ ተብለው ወደ ተለያየ አገር ከሚላኩት አንዱና ዋናኛው ነው። የሥራ ነገርም ከተነሳ ለብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች የሥራ እድል ሰጥቶዋል ወይም ከፍቶዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። የቡናን ውለታ ለመክፈልም የሁን ስሙን እንደ ማስታወሻ ለመጠቀም ቡድናቸውን በሱ ስም ሰይመው ወደ እስቴዲዮም ብቅ ካሉ ሰንበትበት ብለዋል። ምን ይኼ ብቻ ዘፈኑስ ቢሆን ቡና በየዳንኪራ ቢቱም ሆነ ኮንሰርቱ ሳትሞካሽና ሳትወደስ የቀረችበት ጊዜ የለም።

እኔ እንኳን ዛሬ ለመፃፍ የተነሳሁት ስለ ቡና ታሪክ ወይም ስለ ቡና ንግድ ሳይሆን ከቡና ጋር የትና መች እንደተዋወቅን፤ ባለፍኩበት የህይወት ጎዳና ቡና ምን ትዝታ ጥላብኝ

እንዳለፈች፤ አሁን ደግሞ ባለሁበት አካባቢ ያለን ቅርበትና ግንኙነት ምን እንደሚመስል በትዝታ መልክ ለመግለፅ ፈልጌ ነው።

ምንም እንኳን ለአጻጻፍ እንዲመቸኝ ብዬ ቅደም ተከተሉን ባዘጋጅም የተለያዩ የትዝታ ክፍሎቼ ከኔ ጀምር የኔ ትዝታ ይበልጣል እያሉ አተካሮ ገጥመውብኛል። አንዱ ክፍሌ የዛሬ ጫማ ማድረግህን ሳይሆን ቡናን ድሮ ቁምጣ ስታደርግ ባዶ እግርህን ስትሄድ ስለምታውቃት አድባሩም ቄዬውም እንዳይታዘብህ ትዝታህን ከዛ ጀምር ሲል፤ ሌላው ደግሞ ዘመናዊ ነኝ የሚለው ክፍሌ በድሮ በሬ ያረሰ የለም አድባር ቄዬ ገለመሌ ከምትል ትዝታ አለኝ ካልክ አሁን ካለህበት አካባቢ ጀምረህ ቸክችክ ሲል፤ ስፖርት የሚወደው ጎኔ ደግሞ ምነው ስቴድዮም ውስጥ የ "ቡና" ደጋፊ ነኝ እያልክ ላንቃህ እስከሚላቀቅ ትጮህ አልነበረም ታዲያ ያ ሁሉ በቁና የሚሰፈር ትዝታ እያለህ ከዛ ለመጀመር ምን አስፈራህ ሲል፤ ይሄ ዘፈን የሚወደው ክፍሌ ደግሞ እኔ ጥሩ የሆነ አስታራቂ ሀሳብ አለኝ ሁላችንም እንዲያስማማን የጽሑፍህን አርዕስት "ቡና" በለው እንጂ እኔ ግጥም እሰጣለሁ አንባቢዎችህም እየዘፈኑ እንዲያውም ሳይሰለቻቸውና ሳይታወቃቸው ፅሁፍህን አንብበው ይጨርሳሉ ሲለኝ መልካም እንግዲህ ብዬ በዘፈኑ ለማጀመር ተስማማሁ። ከወዲሁ እንግዲህ "ቡና ይፈላ ቡና" ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ የገጠመውን ወይም የገጠመችውንና የዘፈነውን ወይም የዘፈነችውን እያመሰገንኩና ፍቃድ እየጠየኩ ወደ ዘፈኑ እመለሳለሁ።

ቡና ይፈላ ቡና  
አይሰማም ሁላችንም አንድ ላይ  
ቡና ይፈላ ቡና  
ቡና ይፍላ ቡና  
አይ የቡና ሽታ አይነሳ ሱሱ  
ዱካኩስ መች ያስተኛል እሱን ካልቀመሱ  
ቡና አይ ቡና  
ቡና ይፈላ ቡና  
ቡና ይፈላ ቡና  
ጎረቤትም ጥሩ ቡናውንም ጠጡ  
እኔም ፅሁፌን ልጀምር እነንተም አድምጡ  
ቡና አይ ቡና

ከቡና ጋር የቀረበ ግንኙነት የጀመርኩት ገና አንድ ፍሬ ልጅ ሳለሁ ነው። ጡጦው ቀርቶ ቡና እየጠባሁ ነው ያደኩት እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ ማለቴ ልጅ ሆኜ ስላላክ ለማለት ፈልጌ ነው፡ "ልጆች እስኪ ሮጥ ብላችሁ ቡና ገዝታችሁ ኑ ከነጋ ምንም አልቀመስኩም" ትላለች አያታችን ነብሷን ይማርና፡ አቤት ቡና ለመግዛት ያለው እሽቅድምድም ምን እኛ ብቻ የሠፈሩ ልጅ በሙሉ ሳያጉረመርም የሚቀበላት ትዕዛዝ ቢኖር ቡና መግዛትን ነው ለምን መሰላችሁ ለ "ምርቃቷ" ሲባል ነው። ምርቃት ስላችሁ እደግ፤ ተባረክ፤ ኮሌጅ በጥስ አይደለም ባለ ሱቁ በነፃ የሚሰጠን ከረሜላ ነች ሰሟም "ኮሾ" ከረሜላ ትባላለች።

ኮሾን ለማታውቁ የከረሜላ ዝርያዎች ስትሆን በእርግማን ይሁን ወይም በድምፅ ብልጫ ተሸንፋ አይታወቅ ብቻ እንዳትሸጥ በነፃ እንድትታደል የተፈረደባት ነች። ማንኛውም ባለ ሱቅ ደንበኞቹ ከመደብሩ የተለያየ ሸቀጣ ሸቀጥ ከገዙት በተለይ ልጆች አብረው ካሉ ኮሾ ከረሜላን በምርቃት መልክ በነፃ የመስጠት የውዴታ ግዴታ አለበት። ይገዛሉ ከሚባሉትና በየቀኑ ልጆችን ወደ ሱቅ ከሚያስሮጡት አንዱና ዋናው የ "ቡና" ግዢ ስለሆነ በዘህ አጋጣሚ ኮሾ ከረሜላ ልጆች በህጻንነታቸው ከረሜላ እንዲለምዱና መታዘዝን እነዲወዱ የበኩሏን አስተዋፅኦ አድርጋለች በዚያው መጠነ ደግሞ የአንዳንዶቹም ጥርስ እንዲበላሸና ያለ ጊዜው እንዲወልቅ ምክንያትም ሆናለች። ኮሾ ከረሜላን ከሌለው ለየት የሚያደርጋት---እንደሌሎቹ ለየት ባለ ወረቀት ወይም ላስቲክ ጠቅልሉኝ ብላ ቅሬታ የለማሰማቷና መደርደሪያ ለይ የ ክብር ቦታ ካልተሰጠኝ ብላ አካኪ

ዘራፍ ያለማለቷዎ ሲሆን በተጨማሪም የሱቁም ባለቤት ስለማትሸጥ ነው መሰለኝ ሲፈልግ ባንኮኒው ሥር ካልሆነም ሰወር ያለ ቦታ ነው የሚወሸቃት። ለነገሩ ሲሰጠነም በክብር ሳይሆን ወይ ወርውሮ ስንቀልባት ሌላ ጊዜም መሬት ለይ ወድቃ ጠራርገን ስንቆረጥማት ብቻ በቀን በቀን እንደታዘዘ ኪኒን ካልወሰድናት እንደቡና ሱስ ባያዛጋንም ሚፏሽካችን አይቀርም። አሁን ወደ ኋላ ሄጄ ሳስበው የ "ቡና ገቢያ ድርጅትና" የ "ከረሜላ ፋብሪካ" ሆን ብለው ተሻርከው ይሆን ንግዳቸውን ከፍ ለማድረግ ወላጅና ልጆችን በመራራን በጣፋጭ ነገር በሱስ እንዲጠመዱ ያረጉት እላለሁ!።

ቡና ይፈላ ቡና
ቡና ይፈላ ቡና
ተጫዋች ነኝ ብለህ ታኬታ አርገህል
ታዲያ በመቀስ ምት እንዴት ጎል ማግበት ያቅትሀል
ቡና አይ ቡና
ቡና የፈላ ቡና
ቡና የፈላ ቡና
ሂሪጎሬም ስጠው በረኛውም ውጣ
ሰው ብለህ አትጥራኝ ፎሪ ባታወጣ
ቡና አይ ቡና

አካሄዴ ወዴት እንደሆነ ሳይገባችሁ አይቀርም፡ መቼም እየታደገ ሲመጣ የፍላጎትም ይሁን የስሜት ጉዳይ ብቻ አንዳንዱ ስፖርትን እንደጊዜ ማሳለፊያ ሲያዘወትር ሌላው ስፖርትን ከጊዜ ማሳለፊያነት ፍቆ ያወጣው ለራሱ ወይም ለራሷዎ እንደሚስማማው/እነደሚስማማት ወደ ትያትር ወይም ፊልም ቤት መሄድ፤ መፅሐፍ መንበብ፤ ጫት መቃም፤ ድራፍት መለጋት፤ ከረንቡላ መጫወት፡ ዕቁብ መጣል ሌላም ላላም እንደጊዜ ማሳለፊያ ሲዘወተሩ ይታያል።

የኔ እንኳን የዘሬ ትዝታዬ ወደ እግር ኳሱ ላይ ነው የሚያደላው። ስለ እግር ኳስ ብዙ አውቃለሁ ባልልም መቼም ትዝታዬን በማውቃትና በምችላት መንገድ መግለጽ የምችል ነው የሚመስለኝ፡ ከወዲሁ እንግዲህ ለተጫዋቾቹ፤ ለአሠልጣኞቹ፤ ክለቡን ወክለው ለሚጫወቱበት ድርጅት፤ ለዳኞቹ፤ ለአራጋቢዎቹ፤ ለተመልካቾቹ፤ ለፌደሬሽኑ፤ ክለቦችን በግልም ሆነ በድርጅት ለሚረዱት በአጠቃልይ እግር ኳስን ጥሩ የጊዜ ማሳለፊያና የገቢ ምንጭ እንዲሆን ላደረጉትና ለተባበሩት በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

እውነቱን ተናግሮ.... ይባል የለ፤ ምንም እንኳን አንደኛ ዲቪዝዮን ውስጥ ላሉት ለሁሉም ክለቦችና ተጫዋቾች ትልቅ ክብርና አድናቆት ቢኖረኝም በተለይ ለ "ቡና" የእግር ኳስ ክለብ ለየት የለ ስሜት አለኝ---የቴክኒክ ችሎታቸውና የአካል ጥንካሪያቸው፤ አጠቃቃቸው፤ አከላከላቸው፤ በረኛው፡ ወኔያቸው፤ በራስ መተማመናቸው፤ ምንም እንኳን ስፖርት ማሸነፍና መሸነፍ ቢሆንም ሽንፈት ካለ በፀጋ መቀበላቸው፡ ማልያቸው ብቻ ምነ አለፋችሁ በአጠቃላይ ለ እግር ኳስ የሚያሳይቱ ፍቅርና ለማሊያቸው የሚያደርጉት ጫወታ አሁን ድረስ ከ አእምሮዬ አልጠፋም ምንም እንኳን ጫወታቸውን ካየሁና ከሀገር ከወጣሁ አንድ የጠበደል ጎረምሳ ዕድሜ ቢሆንም።

በተለይ ቡናና ጊዮርጊስ ይጋጠማሉ ከተባለ ግጥሚያው ለዋንጫ ከሆን ወሬው ሁሉ ማን ያሸንፋል ነው? በስንት ጎል? ምክንያቱም በጊዜው በጣም ተፎካካሪ ከሚባሉት ክለቦች አንዱና ዋነኞቹ ናቸው፤ ለነገሩ ለብሔራዊ ቡድንም ቢሆን አልፍ አልፎ አንዳንድ ተጫዋቾ ከሌላ ክለብ ቢመረጡም በብዛት ግን ከነዚሁ ከሁለት ቡድኖች ነው የሚወሰዱት። እሁድ መቼም አረዛዘሚ በደጋፊዎች መካከል ያለው ቀልድ ወይም ፍተላ ልበለው መቼም አያድርስ ነው፡ ምን እሱ ብቻ ውርርዱስ ቢሆን! ኪሱን የተማመነው በገንዘቡ፤ ብዙ ሳንቲም የሌለው በድራፍት ምንም የሌለው ደግም በኩርኩም ሲወራረድ ኸረ ምኑ ቅጡ......

ቡና ይፈላ ቡና
ቡና ይፈላ ቡና
በረኛ ነኝ ብለህ አንድ ቁጥር ለብሰህል
ታዲያ ኳሷ በቀኝ ስትገባ አንተ በግራ ምን ያስተኛኽል
ቡና አይ ቡና

እንደማይደርስ የለም እሁድ ይደርሳል ያገኘ ከቤቱ ቁርሱን ቀማምሶ ሲወጣ፤ ሌላው እንደዚሁ እንዳቅሙ ወደ ተለያየ ቦታ ጎራ ብሎ ሲመገብ እንደኛ አይነቱ ደግሞ አጋጭተን ያቺ የተለመደችውን “ፍርፍር” ወይም የጠበቃ ምግብ ጎራርሰን ወደ ስቴዲዮም ለመግባት ሳይሆን ለመሰለፍ እንኳትናለን፡ አንዳንዴ ወደ እስቴዲዮም ለመግባት ተሰልፈን የምናጣፋው ጊዜና የጫወታው ጊዜ ሲተያይ ያለ ማጋነን ሶስት አራት እጅ ይበልጣል ያ አልበቃ ብሎ ደህን ተሰልፈን ስንትና ስንት ሰዐት ቆይተን የትኬት መቁረጫው መስኮት ከፈት ሲል ከየት መጡ ሳይባል ሰርጎ ገቦች ሰልፉን ሲበትኑት ቀደም ተከተሉ ጠፍቶ ፊት የመጣው ኋሏ አሁን የመጡት ፊት ሲሰለፉ ይግባኝ የሚባልበት ጠፍቶ አኩርፎ ወደ ቤት ይኬዳል ሲባል ሞተን እንገኛለሁ ይህን ጫወታ ካላየን ብለን ተመልሰን እዛው ሰልፍ ላይ….

መቼም እንደማይጀመር የለም ጫወታው ይጀመራል በሌላ በኩል ደግሞ የቲፎዞው ተረብና ፍተላ በዚያው መጠን ይቀጥላል ከተጫዋቾቹ አንስቶ እስከ ዳኛው አራጋቢው የሚቀርለት የለም። ትገባለች የተባለችው ጎል ስትሳት…ጎሉን አዙሩለት፤ አየሩ ከብዶት ነው፡ ዳኛው ደግሞ የገባችውን ጎል ሲሽር ወይም ያዳላ መስሎ ከተየ የኼም በይግባኝ ሳይሆን እዛው ሜዳ ላይ አሉ የተባሉት የስድብ ውርምታዋች ሲወርዱ ይሰማል…ጉቦ ወስዶ ነው፤ ለምን አሥራ ሁለተኛ ተጫዋች ሆነህ አትጫወትላቸውም፤ ሜዳውን ለቃችሁ ውጡ፤ ቆይ ትገኛለህ የምታመሽበትን እናውቃለን፡ የ ሁሉ ደግሞ አልፎ እንደዚያ ሲሳደብ የነበረው ቡድኑ ሲያጠቃ…የተወለደበትን ቀን አስቆጥረው፤ መሃል በገባ አጫውቱት፤ በረኛው ላይ በላይነን አስገባ እነዲህ እየተባለ ተጫዋቾቹን ወኔ በወኔ ካደረጉ በሁላ ጎል ከገባች ተደበላለቀ ነው የምላችሁ…ኳሱን ከጎል ውስጥ ዳኛው ያውጣው፤ ጊዜ ግደሉ፤ ጥሩ የተባሉት ተጫዋቾች ደግሞ እንዳይሰበሩና ለሌላ ግጥሚያ እንዲሰለፉ ቀይረው፤ ባጋጣሚ ደግሞ ኳስ ፎሪ ወጥታ እነዚሁ ቲፎዞ ማሃል ከገባች ማን ኳሷን ሊመልስ ተጫዋቹ ቢጠብቅ ዳኟውም ሆነ አራጋቢው ቢመለከቱ ኳስዋን ይዘው ፀጥ ያ አልበቃ ብሎ ተጫዋቹን እሰከ አፍንጫው ልክ ልኩን ሲነግሩት በንዴት አፀያፊ ነገር ተናግሮ ወይም በእጁ መጠፎ ምልክት አሳይቶ የተወሰኑ ጫወታዎች በፀባይ ጉድለት ተብሎ እንዳይጫወት ይታገዳል።

ይሂ ሁሉ አልፎ ደግሞ የክለቦች ግጥሚያ ለጊዜው ጋብ ይልና ብሔራዊ ቡድናችን ግጥሚያ ካለው የ እስቴዲዮሙ መንፈስ ቀየር ይላል። አሁን ሙሉ ስቴዲዮም ለአንድ ቡድን ነው የሚያግዘው፤ ተጫዋቾቻችን አንድ ባንዲራ ወክለው ነው የሚጫወቱት፤ ስቴዲዮም ውስጥ ጫወታውን ማድነቂያም ሆነ ድሉን ማብሰሪያ አንድ ቋንቋ ነው፤ አጠገብ ያለው ወይም ከፊለፊት ይሁን ከኋላ የቆመው የመድን ፤ እርሻ ሰብል፤ አየር ሃይል፤ ምድር ጦር፤ መብራት ሃይል፤ ፖሊስ ሠራዊት፤ ጊዮርጊስ ወይም የቡና ደጋፊ የሁን አይሁን የሚታወቅ ነገር የለም ለዚያም ግድ የሚሰጠው ሰው የለም ተቃቅፎ ብቻ ያንን አረንጓዋዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራችንን ይዞ መጨፈር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የተቃራኒው ቡድን  ሀገሩ ላይ ብሔረዊ ቡድናችንን ስፖርታዊ ጨዋነት የጎደለው ተግባር ፈጽሞ ከሆነ ከተመልካቹ (ከህዝቡ) የመልስ ምቱንም የሚያገኘው የዚያኑ ዕለት ነው። ለዕለቱ የተዘጋጁት ድንጋይም ሆነ ሌላ ነገር ወደ ስቴዲዮም ባስደናቂ ሁኔታ ከገቡ በሁዋላ ትዕዛዝ እሰከሚሰጣቸው ድረስ በተጠንቀቅ መጠባበቅ ነው፡ ከዚያ ወኔውም ተጨምሮ የ ሀገር ጉዳይም ስለሆነ እነዚያ ድንጋዮች መተኮስ የጀምራሉ፡ ተቃራኒውንም ቡድን ይሁን የወከለውን ሀገር ጥሩ ማስታወሻ ከጥሩ ትዝታ ጋር ሰጥቶ ከእስቴዲዬም ማሰናበት ነው፡ አንደንዴ ደግሞ ትዝታው ቶሎ እንዳይጠፋ ያረፉበት ሆቴል ሂዶ የኛ ጫወታ ገና ተጀመረ እንጂ መች

አለቀ እየተባለ መግቢያ መውጫ ማሳጣት ነው፡ ያ አልበቃ ብሎ አውሮፕላን ማረፊያ የቅሌት አሸኛኘት ከተደረገላቸው በሁዋላ ኢትዮጵያ ለይ ምን እንደተፈረደ ዜና መከታተል ነው።

ቡና ይፈላ ቡና
ቡና ይፈላ ቡና
የሠፈሩ ሜዳ የጎል እንጨት የለው
ከበረኞቹ በስተሁዋላ የቆሙት መሰሶዎች ጥቅማቸው ምንድነው ብሎ ሰውን በሳቅ ፈጀው
ቡና አይ ቡና

ኳስ አርግዛ አልገባ ስትል፤ በረኞች እየተወነጨፉ ኳሷን ሲቀልቡ፤ እግር አልስተካከል ብሎ የጎሉን አግዳሚ ብረት ሲቀጠቅጥ፤ ተመልካች ደንዝዞ የምሥራች የምታበስረውን ጎል ሲጠባበቅ፤ ጋዜጠኛው ለኳስ ባለው ፍቅርና በሀገር መውደድ ብቻ ካአሰልጣኙ በላይ የሚሰጠው የ አሰላለፍ ስልት፤ ጫወታውን ለማየት ከገቡት ውስጥ አንዳንዶቹ ከእንግዲህ በሃላ የጎል ዕድል አንጠብቅም እያሉ እያኮረፉና ተጫዋቾቹን እየተራገሙ የሚወጢት፤ በገንዘብ እጦትም ሆነ በስቴዲዮሙ መሙላት ከውጪ ሆኖው የመጨረሻው የማለቂያው ፊሽካ እስካልተነፋ ድረስ ጫወተውም አላለቀም ብሔራዊ ቢድናችንም አልተሸነፈም ብለው በድፍረትና ሙሉ በሙሉ በመተማመን የድሉን ጎል የሚጠባበቀው፤ ገሚሱ ሬድዮ ላይ ጆሮውን ተክሎ ሲጠባበቅ፤ ሌላው የቲቪው እስክሪን ላይ ዐይኑን አፍጥጦ ሲመለከት፤ የኳስ ፍቅር የሌለው ግርግር ስለሌለ ጁተኒና ከረሙቡላ መጫወት ዛሬ ነው እያለ ድንጋዮቹን እርስ በእርስ ሲያጋጭ፤ በመጨረሻ ጋዜጠኛው የተቃጠለ ሰዐት ከሌለ በስተቀር ጫወታው ሊፈፀም በጣም ጠቂት ደቂቃዎች ነው የቀሩት…አሁን የተቃራኒው ቡድን እያጠቃ ነው ኳሷን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን እኛ ሜዳ ላይ ነው የሚጫወቱት፡ በተልይ ስምንት ቁጥርና አሥር ቁጥር ለብሰው የሚጫወቱት በጣም አደገኞች ናቸው  አሁን አሥር ቁጠሩ የዞዋል በ አጭር አድሮጎ ለዘጠኝ ቁጥር ሰጠው ዘጠኙ መልሶ ለ አሥሩ ሰጠው አሥሩ የሗውል እያታለለ ነው ቧጭር አድርጎ ለስምንቱ ሰጠው የኼን ተጫዋች ካልያዙት በጣም አደገኛ ነው አሥራት አጠገቡ አለ ትከሻ ለትከሻ እየተጋፉ ነው ደኙ (ዳኛችው) ከፊት ለፊት አለ ተካበ (በረኛው) ወጣ ብሎ ጎሉን አጥብቦበተል አሥራትን አልፋለሁ ብሎ ኳሷን ወደፊት ስገፋ ዳኛችው ደርሶ ኳሱን አስጥሎተል ዳኙ ኳሱን ይዞ ወደፊት እየገፋ ነው በርቀት ለሙሉጌታ ከበደ አሽጋገረለት ሙሌ አንዱን ተጫዋች ሸወዶ በቀኝ በኩል ላለው ለሙሉጌታ ወልደዬስ አቀበለው ወደፊት እየገፋ ነው ሙሉጌታ ወልደዬስ በአጭር አድርጎ ለገብረመድህን ሰጠው ገብሬ መልሶ ለሙሉጌታ ሰጠው ሚሊዬን በጋሻው በቀኝ ክንፍ እየሮጠ ነው ሙሉጌታ ወልደዬስ ያየው ይመስላል ኳሷን በርቀት አሽጋገረለት ሚሊዬን በደረቱ ካቆመ በሃላ ወደፊት እየገሰገሰ ነው፡ የተቃራኒው ቡድን ተከላካይ ሸርተቴ አስመስሎ የሚሊዬንን እግር ለመምታትና ኳስዎን ለመውሰድ ያደረገው ሙከራ አልተሳካለትም ሚሊዬን ባስደናቂ ሁኔታ ተከላካዩን ዘሎ ኳሱን በቁጥጥር ሥር አድርጎዋል ወደ ጎል የሚያሻማ ይመስላል ሁለቱ ሙሉጌታዎች ገብረመድን እንዲሁም የተቃራኒው ቡድን ተከላካዮች በሙሉ ጎል ውስጥ ናቸው ኳሷን ወደ ጎል አጠፋት ኳሷ በአየር ላይ ነች በቴስታ ገደገደለት ኳሷን ከመረቡ ጋር አዋሀደለት…ጎል ጎል ጎል ጎል ጎል። በኔ ሰዐት አቆጣጠር የጫወታው ጊዜ አልቆዋል ዳኛው ሰዐታቸውን እያዩ ነው ፊሽካ የሚነፉ ይመስላል ነፉ። የጫወታው ጊዜ በብሔራዊ ቡድናችን አሸናፊነት ተጠናቆዋል።

እንዲህ ነው ጫወታ እንዲህ ነው
እንዲህ ነው ጫወታ እንዲህ ነው
እንዲህ ነው ጫወታ እነዲህ ነው
ብራምባር ሰበረልሆ

ብራምባር ሰበረልሆ
ሆ ሆ ሆ ሙሌ ልጅሆ
ብራምባር ሰበረልሆ
ብራምባር ሰበረልሆ
ሆ ሆ ሆ ገብሬ ልጅሆ
አያ ሆ ሆ ማታ ነው ድሌ
ድሌ ማታ ነው ድሌ
አያ ሆ ሆ ማታ ነው ድሌ
የ ኢትዮጵያ ልጅ የሂ ነው አመሌ
አያ ሆ ሆ ማታ ነው ድሌ

ስቴዲዮሙ ተነቃነቀ ነው የምላችሁ። ከክብር እንግዳው አንሰቶ እስከ አስፋው ቂቤ (ይቅርታ እውነተኛ ስማቸው ይሁን አይሁን የማውቀው ነገር የለም እስቴዲዮም ውሰጥ ግን በዚህ ስም ነው የሚጠሯቸው) በግራና በቀኝ ክንፍ የሌት፣ ቲሪቡን ካታንጋና ጥላ ፎቅ የተቀመጡት ተመልካቾች ያንን አረንጓዴ ብጫ ቀይ በንዲራችንን የዘው ሲያውለበልቡት ላየ ስቴዲዮም ውስጥ ሃይለኛ አውሎ ንፋስ የገባ ነው የሚመስለው፡ ምን እሱ ብቻ ድሉን ለማብሰር በተጠንቀቅ የሚጠባበቁት ጋዜጣና ሽሚዞችም ለኩሱን ብንቃጠልም ብንነድም ለሀገራችን ነው የሚሉ ነው የሚመስለው የንን ስቴዲዮም በብርሃንና በሙቀት ሲያደምቁት። ከእስቴዲዮም የሚወጣውም ሆነ ውጪ የሚጠባበቀው የእግር ኳስ ድል የሀገር፣ የአንድነት፣ የባንዲራ ድል ነው ብሎ ስለሚያምን ሁሉም እየጨፈረ ወደ ቤቱ አቅጣጫ የሚወስደውን መንገድ ይዞ በቸርኬ (በእግር) ማቅጠን ነው። አንዳንዱማ ከደስታ ብዛት ሞቼ እገኛለሁ ካልጋበዙክ ብሎ ድራፍት ቤት ጎትቶ ማስገባት ነው የሚቀረው። ስለ ስቴዲዮም ተወርቶ አያልቀም እነዲያው ብትፈቅዱልኝ ለስቴዲዩም ያለኝን ፍቅርና ትዝታ በግጥም ባስነካው ምነ ይመስላችኋል? ፍቃዳችሁ ከሆነ እንግዲህ የውላችሁ…

ስቴዲዮም ልበልሽ ካምቦሎጆ
የትኛው ይሻላል የኔ ቆንጆ
የፈለግሺውን ንገሪኝ በፈለክሺው ልጥራሽ
ትዝታሽ ብቻ አይደለም አለብኝ ውለታሽ
ንገሪኝ እውነቱን ሳትደብቂኝ
ምነ ላምጣ ምን ልታዘዝ እስኪ ንገሪኝ
አሁነ ማን ይሙት አልቆሰለም ገላሽ
ያን ሁሉ ዘመን ሰው ተቀምጦ በጀርባሽ
ታዲያ ምንድነው ዝምተው መታሺያ ላምጣልሽ ወይስ ወጌሻ
የደከመ ሰውነትሽን ማሻ
ወይስ መረቁ ይሻላል ቅልጥሙ
የተለያዩ ክፍሎችሽ እንዲገጣጠሙ
ንገሪኝ ገላልጠሽ ሚስጥር ከእንግዲህ የብቃ
እኔም ቆርጫለሁ ወደ ኋላ ላልል በቃ
ሀገር ሲነሳ አንድነት አንድነት ሲነሳ ባንዲራ
እዚያው አንቺ ሜዳ ተስተናግደው የለ በተራ
አረ ስንቱን ትቼ ስንቱን ላውራ
አያ ሆ ሆ ማታ ነው ድሌ እንዲህ ነው ጫወታ
የተባለው እዚያው አንቺ ቤት አይደል አንቺ ቦታ
ታዲያ እንዴት ተደርጎ ውለታሽ በምን ይከፈላል
ባርኔጣዬን አንስቼ አመሰግናለሁ ብል ይሻላል

ቡና ይፈላ ቡና
ቡና ይፈላ ቡና
ግራንዴንም እዘዝ ኮፊ ላቴንም ጠጣ
ማክያቶን የሚያክል የለም የመጣው ቢማጣ
ቡን አይ ቡና

ቡና እዚህ ባለሁበት አካባቢም ጓደኝነቷ አልተለየኝም ቤትም ተፈልቶ ሆነ ውጪ ጎራ ብዬ መሃዛዋን አሸትቼም ሆነ ቀምሼ ሳልወጣ የቀረሁበት ጊዜ የለም። የጣዕም ነገር ከተነሳ ግን አንዳንዴ እውነት እቺ አብራኝ ያደገች ቡና ነች እያልኩ መጠራጠሬ አልቀርም፡ ጥሬው ተገዝቶ ቤት ተቆልቶ ቢፈላ ወይም ከውጪ የተፈላው ተገዝቶ ቢጠጣ አንድ ልገልፀው የማልችለው የቀራት ንጥረ ነገር አለ ቢሆንም የኢትዮጵያ ቡና የሚለው ራሱ ለኔ በቂ ስለሆነ ልርቃት አልሞከርኩም። አንዳንዴ ደግሞ የቿው የኮሾ ከረሜላ ጓደኛዬ እዚህ ሰው ሀገር መጥታ በዘር በሃይማኖት ከማይገናኙት ነገሮች ጋር ተደበላልቃም ስትሰራ ታሳዝነኛለች፤ አቤት ላሻሻጥ እንዲመቻቸው የሚሰጧት ስምስ!! እስኪ አንድ ቀን ወደ ባሪስታው አጠገብ ጠጋ ብላችሁ የሚሰጡትን ትዕዛዝ አድምጡ ጉድ ነው የምትሉት....ቶል ሞካ፤ ቬንቲ ካርሜል ማክያቶ፤ አይስድ ቬንቲ ቫኒላ፤ ነን ፋት ላቴ፤ ዱብዬ ማክያቶ፤ ካርመን አፕል ሲደር፤ ሾርት ካፑቺኖ፤ ግራንዴ ቨንቲ ላቴ፤ ነን ፋት ላቴ፤ ግራንዴ ኮፊ፤ ቶል ኮፊ፤ ሾርት ኮፊ፤ ስሞል ኮፊ ወዘተ.. ምን ይኼ ብቻ የተደረደሩትን የሲረፕ ጠርሙስ ለተመለከተ የኬሚስትሪ ላብራቶሪ የገቡ እንጂ ቡና መጠጫ ወይም ኮፊ ሾፕ የገቡ አይመስልም።

ቡና ይፈላ ቡና
ቡና ይፈላ ቡና
ትዝታዬንም ጨረስኩ ፅሁፌንም ለቁም
እኔ ልሙት ባልልም በድጋሚ መገናኘታችን አይቀርም
ቡና አይ ቡና
ወይ ቡና

በሉ እንግዲህ አልያዛችሁ ደህና ሰንብቱ እኔም ቡናው ነው መሰለኝ እያንገላጀጀኝ ነው ሄጄ አንድ ሲኒዬን ላፍ ላድርግ።

Copyright@2004-2005, Bekele Gebriel